SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

| | | |
|---|---|---|
| 1[ki] Diro Kiiro 11<br>Hawassa, Maaja 7, 2012 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Amaale Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho<br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፩<br>ሀዋሳ ሐምሌ ፯ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም |


**Amado**

**Lallawu Kiiro 11/2012**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Sidaamu Tuqu Xaadooshshi Uurrinsha Biilloonyenna Loosu Queecha Murate Fulino Lallawa**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፲፩/፳፻፲፪**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሲዳማ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ**

## Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Sidaamu Tuqu Xaadooshshi Uurrinsha Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa

Qoqqowu Bayriidi Seerinni worroonni garinni babbaxxitino hedonna lao dagoomu giddo harase buuxate kaajjado uurrinshatenna loosu wolapho hattono seeru agarooshshe afirino qoqqowu mootimma annimmanni massagamanno tuqu xaadooshshi uurrinsha uurrisa hasiisasenni qoqqowu Jeefisiisaanote Bisubba Uurrisate, Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa Kiiro 3/2012 quwa 11 cinaancho quwa 3 garinni Sidaamu Tuqu

## የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሲዳማ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በክልሉ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሠረት የተለያዩ ሀሳቦችና አመለካከቶች በሕብረተሰቡ ውስጥ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ የተጠናከረ የተቋምና የአሠራር ነጻነት እንዲሁም የሕግ ጥበቃ ያለው በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት የሚመራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋም በማስፈለጉ በክልሉ የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 3/2012 አንቀጽ 11 ንዑስ

Xaadooshshi Uurrinsha uurrinsoonniha ikkasinni,

Uurrinsoonniti Sidaamu Tuqu Xaadooshshi Uurrinsha lophitanni daggino kalqetenna gobboomu rakkino mashalaqqete soorro hasatto hedote giddo worite dagoomunnita barru barru millimmo gambissenna hala'ladunni xawisatenni fultara dandiitanno qeecha huwatatenni ikkadimmatenni tantanante gobbate giddo heedhanno wolootu tuqu xaadooshshubba ledo heewisamaancho ikkite yawose woyyaawino deerrinni fultara biiilloonyenna loosu qeecha mura hasiissinohura,

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaale Mini Qoqqowu Bayriidi Seera quwa 48 cinaancho quwa (3) (a) nna Jeefisiisaanote Bisubba Uurrisate, Biilloonyenna Qeecha Murate Fulino Lallawa Kiiro 3/2012 quwa 11 cinaancho quwa (4) hundaanni uyinoonni biilloonyinni aane noohu lallawamino.

## GAFA MITE

## XAPHOOMU WORO

### 1. Harancho Su'ma

Konne lallawa "Sidaamu Tuqu Xaadooshshi Uurrinsha Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa Kiiro 11/2012" yine xawinsara dandiinanni.

አንቀጽ 3 መሠረት የሲዳማ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት የተቋቋመ በመሆኑ፣

የተቋቋመው የሲዳማ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት አለማቀፋዊ እና አገራዊ ፈጣን የመረጃ ልውውጥ ፍላጎት እያደገ መምጣቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሕብረተሰቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች በቅርበትና በስፋት በመዘገብ ሊጫወት የሚችለውን ሚና በመረዳት በብቃት ተዋቅሮና በሀገሪቱ ካሉ ሌሎች የብዙኃን መገናኛዎች ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ ኃላፊነቱን በተሻለ ደረጃ እንዲወጣ ስልጣንና ተግባሩን መወሰን በማስፈለጉ፣

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ (3) (ሀ) እና የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 3/2012 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (4) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሲዳማ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፩/፳፻፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. Tiro**

Qaalu eo wole tiro uyisiissannoha ikka hoogiro lallawi giddo:

1. “Qoqqowo” yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.

2. “Boorde” yaa Qoqqowu Jeefisiisaanote Bisubba Uurrisate, Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa Kiiro 3/2012 quwa 3 cinaancho quwa (3) garinni uurritino Sidaamu Tuqu Xaadooshshi Uurrinsha Looso Massagganno Boordeeti.

3. “Tuqu Xaadooshshi” yaa raadiyoonna televizhiinetenni hattono gaazeexunna maxaafichotenni mashalaqqe gamba assate, qixxeessatenna fincate loossa loossanno odootenna wole addi addi orti pirogiraame loossanna borricho qixxeessatenni addi addi hayyonni dagate fincitanno woy kuri addaattate sayissanno wolootu uurrinshubbara beekkanno uurrinshuwaati.

4. “Odeessaancho” yaa tuqu xaaddooshshi uurrinsha giddo qixxeessaanchimmatenni,

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. “ክልል” ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፡፡

2. “ቦርድ” ማለት በክልሉ የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 3/2012 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተቋቋመው የሲዳማ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ሥራ አመራር ቦርድ ነው፡፡

3. “የብዙኃን መገናኛ” ማለት በሬዲዮና ቴለቪዥን እንዲሁም በጋዜጦችና በመጽሔቶች አማካኝነት መረጃ የማሰባሰብ፣ የማዘጋጀትና የማሠራጨት ሥራዎችን የሚያከናውኑ የዜና እና ሌሎች የፊቸር ፕሮግራም ስራዎችንና መጣጥፎችን በማጠናቀር በልዩ ልዩ ዘዴዎች ለሕዝብ የሚያሰራጩ ወይም እነዚህኑ በቀጥታ ለሚያስተላልፉ ሌሎች ተቋማት የሚያከፋፍሉ ተቋማት ናቸው፡፡

4. “ጋዜጠኛ” ማለት በብዙኃን መገናኛ ድርጅቱ ውስጥ በአዘጋጅነት፣ በዘጋቢነት፣ በአርታኢነት፣ በካርቱን አዘጋጅነት፣ በግራፊክስ ባለሙያነት፣ በፎቶግራፍ አንሺነት፣ በተንቀሳቃሽ

odoote shiqishaanchimmanni, buuxaanchimmatenni, kanki-misilete qixxeessaanchimmanni, giraafikisete ogeessimmanni, foote kayisaanchimmanni, millisanni filme kayisatenni, filmete muccishaanchimmanni, filmete massagaanchimmanni, tekinikete ogeessimmanni woy odootenna mashalaqqe gamba assatenni, orte amadisiisatenna fincate ogimma aana loosanno aye manchooti.

5. "Mancho" yaa aye kalaqamu mancho woy seerunni Mannimmate qoosso uyinoonni bisooti.

6. "Uurrinsha" yaa Sidaamu Tuqu Xadooshshi Uurrinshaati.

**3. <u>Uurrinshate Teesso</u>**

1. Uurrinshannihu qaru borrote mini Hawaasa ikkanno.

2. Hasiise leelliro uurrinshate qoqqowu giddonna qoqqowu gobbaanni sinu borrote minnanna riqiwote borro minna heedhasera dandaanno.

ፊልም አንሺነት፣ በፊልም ኤዲተርነት፣ በፊልም ዳይሬክተርነት፣ በቴክኒሻኒነት ወይም ዜና እና መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማቀነባበርና በማሠራጨት ሙያ የተሠማራ ማናቸውም ሰው ነው፡፡

5. "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

6. "ድርጅት" ማለት የሲዳማ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ነው፡፡

**3. <u>ስለድርጅቱ መቀመጫ</u>**

1. የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት ሀዋሳ ይሆናል፡፡

2. ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ ቅርንጫፎችና ወኪል ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

**4. <u>የድርጅቱ ዓላማዎች</u>**

ድርጅቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በፌዴራሉና በክልሉ ሕገ መንግሥት እንዲሁም በሌሎች አግባቢነት ባላቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ሀሳብን በነጻ የመግለጽ ነጻነትን ማበረታታት፡፡

2. የክልሉ ነዋሪ ለመረጃ ቅርበት እንዲኖረው ምቹ ሁኔታዎችን

4. **Uurrinshate Hexxo**

Uurrinshate aante noo hexxo heedhannose:

1. Federaaletenna qoqqowu Bayriidi Seeri hattono woloota xaadooshshu noonsa polise, seerubba, wodhuwanna biddissuwa garinni hedo ruxxeessu nookkiha xawisate wolapho jawaachisha.
2. Qoqqowu teesaano mashalaqqete mulimma heedhannonsa gede dancha injo kalaqatenni yannittenna halaalu taje afidhanno assatenni qara qara gobboomunna qoqqowu hajubba aana gobboomu sumuumme kalaqate loosa.
3. Qoqqowu miinju, politikunna Dagoomitte milli millo giddo halammete qeecha fultannonna dagoomu giddo dimokiraasichu budi lophanno gede kakkaayisa.

**GAFA LAME**

**UURRINSHATE BIILLOONYE, LOOSU QEECHANNA QOOSSO**

5. **Uurrinshate Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Uurrinsha konninni aane noo biilloonyinna loosu qeechi heedhannose:

1. Qoqqowu dagara horo uyitanno odoonna odoo labbanno mashalaqquwa pireesete gummanni,

በመፍጠር ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃዎችን እንዲያገኝ ማድረግ፣ በዚህም በዋና ዋና የሀገሪቱና የክልሉ ጉዳዮች ላይ ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር እንዲችል መስራት፡፡

3. በክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አጋዥ ሚና መጫወትና በሕብረተሰቡ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ባሕል እንዲጎለብት ማበረታታት፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ስለ ድርጅቱ ስልጣን፣ ተግባርና መብት**

5. **የድርጅቱ ስልጣንና ተግባር**

ድርጅቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለክልሉ ሕዝብ ጠቀሜታ ያላቸውን አስፈላጊ ዜናና ዜና ነክ መረጃዎችን በፕሬስ ውጤቶች፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ማሠራጫዎች ለሕዝብ ያስተላልፋል፤ ለዚህም እንዲረዳው እንደአስፈላጊነቱ መደበኛ የጋዜጣ፣ የመጽሔትና ሌሎች ሕትመቶች እንዲሁም የሬዲዮና ቴሌቪዥን ማሠራጫና ፕሮግራሞች እንዲኖሩት ያደርጋል፡፡
2. የመንግሥትን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች፣ ፖሊሲዎችና ሕጎች

radoonetenna televizhiinete finconni dagate sayissanno; konnira kaa’lanno gede hasiishshu garinni rosamino gaazeexa, maxaafichonna woloota attamishsha hattono raadoonetenna televizhiinete finconna pirogiraame heedhannose assitanno.

2. Mootimmate istiraateejete illachubba, polisenna seera dagate egensiissanno; dagano istiraateejubbate, polisetenna seerubbate aana hedho soorridhanno, maltannonna hedonsano wortanno gede; konninnino gobboommu sumuumme aana iillinanni gede midiiyu bare injo kalaqqanno.

3. Qoqqowu daga maannihiimmatenna dimokiraasitte qoossuwara noonsa huwanyo lossate kaa’litanno addi addi qixxawubba rosichu ledo fiixoonsitanni shiqishshanno.

4. Xalala dagate hedonna qummeessa haadhe koyissanno; hajo la’annonsa bisubbano xa’mite buuxxanno afidhanno gumano dagate xawissanno.

5. Dagate xaphoomu egenno lossitannonna daa”atate hasattonsano wonshitanno addi addi borrichonna radooneteno ikko televizhiinete qixxawubba loossanni babbaxxitino Hayyonni fincitanno.

6. Yannitte ikkitino miinju, polotikunna Dagoomitte hajubba harunsite odeessitanno.

ለሕዝብ ያስተዋውቃል፤ ሕዝቡም በስትራቴጂዎቹ፣ በፖሊሲዎቹና በሕጎቹ ላይ ሀሳቡን እንዲለዋወጥባቸው፣ እንዲመክርባቸውና አስተያየቱን እንዲሰጥባቸው በዚህም ብሔራዊ መግባባት ላይ እንዲደርስ ምቹ የሚዲያ መድረኮችን ይፈጥራል፡፡

3. የክልሉ ሕዝብ ስለሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለውን ግንዛቤ ለማጎልበት የሚረዱ ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ከተሞክሮዎች ጋር እያዛመደ ያቀርባል፡፡

4. ነጻ የሕዝብ አስተያየቶችንና ጥቆማዎችን ተቀብሎ ያስተናግዳል፤ የሚመለከታቸውንም አካላት በመጠየቅ ያጣራል ውጤቱንም መልሶ ለሕዝብ ይገልጻል፡፡

5. የሕዝቡን ጠቅላላ እውቀት የሚያዳብሩና የመዝናናት ፍላጎትን የሚያረኩ ልዩ ልዩ ጽሑፎችንና የሬዲዮም ሆነ የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን እየሠራ በተለያዩ ዘዴዎች ያሠራጫል፡፡

6. ወቅታዊነት ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ተከታትሎ ይዘግባል፡፡

7. በክልሉ ውስጥ የሚፈጸሙ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥረቶችንና ውጤቶችን በተከታታይ በመዘገብ

7. Qoqqowu giddo loosantanno latishshunna gashshootu jawaantenna gumase sufamme noo garinni odeessatenni dahgate egensiissanno; dagate beeqqooshshe lossate looso loossanno.

8. Foototenna milli yitanno misile maareekko, attamunna egensiishshu owaante uyitanno.

9. Loosoho hasiissanno attamu owaante, raadoonetenna televizhiinete pirogiraame qineessonna finco, odoonna mashalaqqe sayisate woy hattono kuri labbanno owaante uyitanno wole uurrinshuwanna udiinnicho hasiissanno basera kaasanno, uurrisanno, tantananno, gashshanno.

10. Uyitanno owaantera taalcho baatooshshe baatisiissanno, Hasiishshu garinni bocunni woy wo’munni wo’ma baatooshshiweelo owaante uyitara dandiitanno.

11. Gobbate seeri garinni gobbate giddoonninna gobbaanni heedhanno labbanno uurrinshuwa ledo odoonna mashalaqqe soorrirano ikko qajeelshanna rosicho soorrirate dandiisiisanno loosu xaadooshshe kalaqidhanno.

12. Gobbate giddonna gobbaanni heedhannonna uurrinshate tekinikete, mashalaqqete udiinnicho woy xaphoomu wolqa kaajjishate irko assate

ለሕዝብ ያሳውቃል፤ የሕዝብ ተሳታፊነትን የማጎልበት ሥራ ይሠራል፡፡

8. የፎቶግራፍና የተንቀሳቃሽ ምስል ዶክመንቴሽን፣ የሕትመትና የማስታወቂያ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡

9. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የሕትመት አገልግሎቶችን፣ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ማቀናበሪያና ማሠራጫዎችን፣ የዜናና መረጃ ማስተላለፊያ ወይም ማሸጋገሪያዎችን እንዲሁም ለተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውሉ ሌሎች ተቋማትን እና መሳሪያዎችን በተገቢው ስፍራ ይተክላል፣ ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፡፡

10. ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፣ እንደአስፈላጊነቱም በከፍልም ሆነ በሙሉ ከክፍያ ነጻ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡

11. በአገሪቱ ሕግ መሠረት በአገር ውስጥና በውጭ አገር ካሉ ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር ዜናዎችንና መረጃዎችን ለመለዋወጥም ሆነ የስልጠና እና የልምድ ልውውጦችን ለማድረግ የሚያስችሉትን የሥራ ግንኙነቶች ይመሠርታል፡፡

12. በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከሚገኙና

umonsa fajjitanno uurrinshuwa ledo qoqqowunna gobbate polisenna seera agarte halante loossanno.

13. Qoqqowu tuqu xadooshshi hala'lannonna sumuu yitanno tekinooloojenni dhaawantanno, lifixanna deerrase agadhitino owaante uyitanno ikkito xiinxallatenni hedo shiqishshanno; fajjinanni yannara loosu aana hosiissanno.

14. Hexxose gafa gansiisate hasiissanno wole seeru fajjanno loossa loossanno.

**6. <u>Uurrinshate Qoosso</u>**

Uurrinsha aante noo qoossuwa heedhannose:

1. Jajju kalaqirate,
2. Su'misenni sheemaate eate,
3. Uyitanno owaantera baatooshshe muratenna gamba assate,
4. Miidiyu guma laashshate, dikko fushshate, laashshino miidiyu gumi annimma, tenne qoosso hirate woy yannate geeshsha baatooshshunni horoonsirannohunnira sayisate.

**<u>GAFA SASE</u>**

**<u>UURRINSHATE TANTANONNA LOOSU MASSAGO</u>**

**የድርጅቱን ቴክኒካዊ፣ ቁሳዊ የመረጃ ወይም ለአጠቃላይ ሁለንተናዊ አቅም ለማጎልበት ድጋፍ ለማድረግ ፈቃደኝነቱ ካላቸው ድርጅቶች ጋር በክልሉና በአገሪቱ ፖሊሲዎችና ሕጎች መሠረት አብሮ ይሠራል፡፡**

13. **የክልሉ ብዙኃን መገናኛዎች ስለሚስፋፋበትና በተስማሚ ቴክኖሎጂ ስለሚደራጁበት፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ስለሚሰጡበት ሁኔታ በማጥናት ሀሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፡፡**

14. **ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፡፡**

**6. <u>የድርጅቱ መብቶች</u>**

**ድርጅቱ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-**

1. **የንብረት ባለቤት የመሆን፣**
2. **በስሙ ውል የመዋዋል፣**
3. **በስሙ የመክሰስ፣ የመከሰስ፣**
4. **ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ የመጣልና የማስከፈል፣**
5. **የሚዲያ ውጤቶችን የማምረት፣ ገበያ ላይ የማዋል፣ ላመረታቸው የሚዲያ ውጤቶች ባለቤት የመሆን፤ ይህንንም መብት የመሸጥ ወይም የማከራየት፡፡**

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**7. <u>Uurrinshate Bisubba</u>**

Uurrinshate aante noo bisubba heedhannose:

1. Loosu Massago Boorde,
2. Qaru Loosu Harisaanchi,
3. Layinki Loosu Harisaanchi,
4. Raadoonete, Televizhiinete, Pireesete, Odoote Owaantenna wole hasiissanno loosu handaarubbanna loosaasine heedhannose.

**8. <u>Boordete Tantanonna Galtino</u>**

1. Uurrinsha lamalunni ajjannokkinna honsunni sa’annokki miilla heedhanno loosu massago boordenni massagantanno.
2. Boordete miillanna gambisaanchu hajote ledo xaadooshshu noonsa mootimmate bisubbanninna dagoomu handaarubbanni filante Qoqqowu Pirezidaantichi shiqisheenna Qoqqowu Amaale Mininni somantanno. Konni garinni:
   a) Mootimmate Kominikeeshiine Biiro Sooreessi…..Gambisaancho
   b) Uurrinshate Loosu Harisaanchi…..Miilanna borreessaancho

**<u>ስለ ድርጅቱ አወቃቀርና ሥራ አመራር</u>**

**7. <u>የድርጅቱ አካላት</u>**

ድርጅቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ፣
2. ዋና ሥራ አስኪያጅ፣
3. ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣
4. የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥን፣ የፕሬስ፣ የዜና አገልግሎትና ሌሎች አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**8. <u>ስለቦርዱ አወቃቀርና ተጠሪነት</u>**

1. ድርጅቱ ከሰባት የማያንሱና ከዘጠኝ የማይበልጡ አባላት ባሉት የሥራ አመራር ቦርድ ይመራል፡፡
2. የቦርዱ አባላትና ሰብሳቢው አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላትና የሕብረተሰብ ክፍሎች ተውጣጥተው በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሰየማሉ፡፡ በዚህም መሠረት፡-
   ሀ) የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ……ሰብሳቢ
   ለ) የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ...........አባልና ፀሐፊ
   ሐ) ከክልል ምክር ቤት አባላት….አራት አባላት

c) Qoqqowu Amaale Mini Miilla…….Shoole Miilla

d) Sivike maamarranni…….Sase miilla heedhannose.

3. Boorde galtannohu qoqqowu Amaale Mini hundaanni ikkanno.

**9. Boordete Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Boordete konni lallawi garinni aane noo biilloonyinna loosu qeechi heerannose:

1. Uurrinshate aliidi massagote biso ikkite loossanno.
2. Uurrinsha tuqu xaadooshshe la’ino polise, seera, wodhonna biddisuwa qoqqowu giddo loosu aana hosase buuxxanno.
3. Daga affara hasiissanno mootimmate polise, seera, wodhonna biddissuwa uurrinshate addi addi tuqu xaadooshshi widoonni yanna yannantenni sa”ase harunsitanno.
4. Uurrinsha uyitanno owaantenni daga mageeshshi geeshsha horaamette ikkitinore yanna yannantenni keentanno; roore

መ) ከሲቪክ ማህበራት…….ሦስት አባላት ይኖሩታል፡፡

3. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ ምክር ቤት ይሆናል፡፡

**9. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>**

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ከፍተኛው የድርጅቱ አመራር አካል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ድርጅቱ የብዙኃን መገናኛዎችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ማድረጉን ያረጋግጣል፡፡
3. በሕዝብ ሊታወቁ የሚገባቸው የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በድርጅቱ ልዩ ልዩ የብዙኃን መገናኛዎች አማካኝነት በወቅቱ መተላለፋቸውን ይከታተላል፡፡
4. ድርጅቱ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች የክልሉ ሕዝብ ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆነ በየጊዜው ይገመግማል፤ ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆንባቸውን መንገዶችም በየጊዜው እየፈተሸ ተግባራዊ እንዲሆኑ ለድርጅቱ አቅጣጫዎችንና መመሪያዎችን ይሰጣል፡፡

horaameette ikkitanno doogga yanna yannantenni faltanni loosu aana hossanno gede raga wortanno, Biddissa sayissanno.

5. Uurrinsha konni lallawi garinni loossanno loossa lainohunni dagatewiinni ka'anno gungummenna shiqqanno koffeenyi aana hasiisanno xawishshi aamamanno gede assitanno; Hasiishshu garinni gungummenna koffeenya buuxxe gumulo sayissanno.

6. Uurrinsha ayimmatenni, koo-teemmatenni, amma'notenninna polotiku laooshshi mereero badooshshe assitukkinni dassitinokki mashalaqqete amado baalunkura aase harunsitanno.

7. Uurrinshate odeessaano, tekinikete ogeeyyenna irko assitanno loosaasine damooza, qixirete, addi addi horo, gumulshu biddissanna loosaasinete gashshooti maanuwaale qixxaabbe shiqqanno gede assite buuxxe kaajjishshanno; loosu aana hossanno gedeno assitanno.

8. Uurrinshate fayinaansetenna jajju gashshooti biddissanna manuwaale qixxaabbe shiqqanno gede assaite buuxxe kaajjishshanno; loosu aana hossanno

5. ድርጅቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚፈጽማቸውን ተግባራት በተመለከተ ከሕዝብ በሚነሱ ስሞታዎችና በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ተገቢ ማብራሪያዎች እንዲሰጥ ያደርጋል፣ እንደአስፈላጊነቱም ስሞታዎችንና ቅሬታዎችን መርምሮ የበኩሉን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

6. ድርጅቱ በማንነት፣ በጾታ፣ በኃይማኖት እና በፖለቲካ አመለካከቶች መካከል ልዩነት ሳያደርግ ለሁሉም ወገኖች ሚዛናዊ የመረጃ ሽፋን መስጠቱን ይቆጣጠራል፡፡

7. የድርጅቱን ጋዜጠኞች፣ የቴክኒክ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የደመወዝ፣ የቅጥር፣ የጥቅማ ጥቅም፣ የአፈጻጸም መመሪያዎችና የሠራተኛ አስተዳደር ማኑዋል ተዘጋጅቶ እንዲቀርብለት በማድረግ መርምሮ ያፀድቃል፣ ስራ ላይ እንዲውልም ያደርጋል፡፡

8. የድርጅቱ የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር መመሪያና ማኑዋል ተዘጋጅቶ እንዲቀርብለት በማድረግ መርምሮ ያፀድቃል፣ ስራ ላይ እንዲውልም ያዛል፡፡

9. የድርጅቱን መዋቅር አቅም በመገምገም ያፀድቃል፤ ስራ ላይ

gede hajajjanno.

9. Uurrinshate tantano wolqa keente kaajjishshanno; loosu aana hossanno gede hajajjanno.

10. Uurrinshannita harancho, mereerimanna seeda yanna hattono dirunnita kapitaaletenna rosantino baajeette mixonna rippoorte kaajjishshanno; jeefishshanno harunsitanno.

11. Uurrinsha mootimmatenninna giddo eonni gaammoonnise baajeette ragunni loosu aana hosiisase illaallissanno, harunsitanno.

12. Uurrinsha kaajjitanno, loosu amanyootino woyyaawanno doogo faashshanno.

13. Uurrinshanniha layinki loosu harisaancho qaru loosu harisaanchi shiqisheenna mootoonsitanno; wole aliidi uurrinshate massagaano miilla filonna gaamooshshe gumultanno.

14. Uurrinsha la’anno wole poolisete hajubba aana maltanno, gumultanno.

**10. <u>Boordete Gambooshshe</u>**

1. Boorde ajanni ajeenna aganunni mitte higge uurrinshate gambooshshe assitanno. Boordete miilla gambooshshu hoshsho baatooshshe Jeefisiisaanote

እንዲውልም ያዛል፡፡

10. የድርጅቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እንደዚሁም ዓመታዊ፣ የካፒታልና መደበኛ በጀት ዕቅድና ሪፖርት ያስፀድቃል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

11. ድርጅቱ ከመንግሥትና ከውስጥ ገቢ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ማዋሉን ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፡፡

12. ድርጅቱ የሚጠናከርበትን፣ አሠራሩ የሚሻሻልበትን መንገድ ይቀይሳል፡፡

13. የድርጅቱን ምክትል ሥራ አስኪያጅ በዋና ሥራ አስኪያጁ አቅራቢነት ይሾማል፤ ሌሎች ከፍተኛ የድርጅቱን አመራር አካላት አመላመልና ምደባ ይወስናል፡፡

14. ድርጅቱን በሚመለከቱ ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ይወስናል፡፡

10. <u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡ የቦርዱ አባላት የስብሰባ አበልም በመስተዳድር ምክር ቤቱ ይወሰናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ ጉዳይ

Amaale Mini gumulanno.

2. Konni quwira cinaancho quwa (1) aana worroonnihu noowa heereenna mudditino haja xaadduro boordete massagaancho woshshattonni woy boordete miilla mereerinni sasetenni mitte anga xa'monni aye yannara gamba yitara dandiitanno.

3. Gambooshshe aana bocu aliidi miilla leelturo songo guutate.

4. Boorde aye gumulo sayissannohu rooriidi huuronni ikkanna huuro taalo ikkitanno yannara gambisaanchu irkisanno huuro boordete gumulo ikkitanno.

5. Boorde konne lallawa harunsite umise Gambooshshunna loosu amanyooti Biddissa fushshitara dandiitanno.

**11. <u>Qaru Loosu Harisaanchi Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

1. Uurrinshate qaru loosu harisaanchi Prirezidaantichunni mootoo'manno.

2. Qaru loosu harisaanchi uurrinshate qara loosu jeefisiisaancho ikke boordetenni uyinanni xaphoomu biddissi garinni uurrinshate looso loosanno, gashshanno.

ሲያጋጥም በቦርዱ ሰብሳቢ ጥሪ ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል አንድ ሦስተኛዎቹ ከጠየቁ በማናቸውም ጊዜ መሰብሰብ ይችላል፡፡

3. በስብሰባው ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

4. ቦርዱ ማንኛውንም ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ሲሆን ድምጽ እኩል ለእኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሀሳብ የቦርዱ ውሳኔ ያሳልፋል፡፡

5. ቦርዱ ይህንን አዋጅ ተከትሎ የራሱን የስብሰባና የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**11. <u>ስለዋና ሥራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር</u>**

1. የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በርዕሰ መስተዳድሩ ይሾማል፡፡

2. ዋና ሥራ አስኪያጁ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ስራ ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ላይ ለድርጅቱ የተሰጡትን ዝርዝር ተግራት እና በተጨማሪም የሚከተሉትን ያከናውናል፡-

3. Konni quwira cinaancho quwa (2) worroonni woro noowa heedheenna loosu harisaanchi konni lallawira quwa 5 aana uurrinshate uyinoonni tittirshu loosu qeechuwanna ledoteno aante noota loosanno:

   a) Uurrinshanniha barru barru loossa aliidimmatenni loosanno, illaallissanno.

   b) Uurrinshate borro mine uurrisanno.

   c) Konni lallawira quwa 9 cinaancho quwa 7 garinni odeessaano, tekinikete ogeeyyenna irko assitanno loosaasine qaxaranno, gashshanno.

   d) Uurrinshannita seeda, mereerimanna harancho yanna hattono dirunnita loosu pirogiraamenna safote baajeette qixxeesse boordete shiqishe kaajjituro loosu aana hosiisanno.

   e) Uurrinshate fajjinoonni baajeettenna loosu pirogiraame garinni woxe fushsha assanno.

   f) Sayikki bisi ledo assinanni xaadooshshi baalaho uurrinsha riqiwanno.

   g) Uurrinshannita loosu millimmo lainohunni yanna agadhitino rippoorte boordetenna Pirezidaantichaho shiqishanno.

ሀ) የድርጅቱን የዕለት ተዕለት ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

ለ) የድርጅቱን ጽ/ቤት ያደራጃል፡፡

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት ጋዜጠኞችን፣ የቴክኒክ ባለሙያዎችንና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፡፡

መ) የድርጅቱን የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ እንዲሁም ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምና የበጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለቦርዱ በማቅረብ ሲወሰንለት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ሠ) ለድርጅቱ በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፡፡

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ድርጅቱን ይወክላል፡፡

ሰ) የድርጅቱን የስራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለቦርዱ እና ለርዕሰ መስተዳድሩ ያቀርባል፡፡

ሸ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

4. ዋና ሥራ አስኪያጅ ለድርጅቱ ስራ

h) Boordetenni uyinanni wole loossa loosanno.

4. Qaru loosu harisaanchi uurrinshate loosi lifinxe hasiisi bikkinni biilloonyenna loosu qeecha booce woriidi uurrinshate loosu sooreeyyeranna wole loosaasinera riqiwo aara dandaanno. Ikkollana, iso riqiwe loosanno manchi 30 barra aleenni ikkitanno yannara riqiwamannoha ikkiro balaxe boordete shiqe kaajja hasiisanno.

**12. <u>Layinki Loosu Harisaanchi Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

1. Layinki loosu harisaanchi qaru loosu harisaanchi aannosi biddissi garinni worosiinni gaammoonni handaarubba looso loosanno, qineessanno hattono qaru loosu harisaanchi aannosi wole loossa loosanno.
2. Qaru loosu harisaanchi heerannokki woy loose afannokki yannara riqiwe uurrinsha massaganno.

**<u>GAFA SHOOLE</u>**

**<u>ADDI ADDI WORO</u>**

**13. <u>Uurrinshate Baajeette Buenna Gashshoote</u>**

1. Uurrinshate baajeette aantino bu'anni fultannota ikkitanno.

a) Qoqqowu Amaale Mininni gaammanni

ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለበታች የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን እሱን ተክቶ የሚሠራው ሰው ከ30 ቀናት በላይ ለሚሆን ጊዜ የሚወከል ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለቦርዱ ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡

12. <u>ስለ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባራት</u>

1. ምክትል ሥራ አስኪያጅ ከዋናው ሥራ አስኪያጅ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በስሩ የተመደቡለትን ዘርፎች ተግባር ይመራል፤ ያስተባብራል፤ እንድሁም ከዋናው ሥራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡
2. ዋና ሥራ አስኪያጅ በሌለበት ወይም መስራት በማይችልበት ጊዜ እሱን ተክቶ ድርጅቱን ይመራል፡፡

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

13. **<u>የድርጅቱ የበጀት ምንጭና አስተዳደር</u>**

1. የድርጅቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡፡

ሀ) በክልሉ ምክር ቤት

baajeette,

b) Konni lallawi garinni gamba assinanni owaantete baatooshshe,

c) Woloota bua.

2. Konni quwira cinaancho quwa 1 hundaanni (a) nni (c) geeshsha xawinsoonni buanni gamba assinanni eo uurrinshate su'minni fannanni baankete shallagora ofollannoha ikkeenna uurrinshate looso loosate yanna yannantenni fushsha assinanni.

3. Uurrinshannita eote hattono udiinnichu gashshootinni horoonshi uurrinshate woxunna udiinnicho gashshooti biddissanna maanuwaale garinni gumulamannoha ikke maanuwaale woyyeessatenna soorrate roorreenyi uurrinshate loosu massago boordeho.

**14. <u>Shallagote Borreessamaasincho</u>**

1. Uurrinsha wo'manna halaalanya shallagote borreessamaasinchonna sanade amaddanno.

2. Uurrinshate shallago qoqqowu qaru qorqoraanchi woy gobbaayidi qorqoraanonni bajeettete dirunni qorqorranni.

**15. <u>Wodhonna Biddissa Fushshate Biilloonye</u>**

1. Konne lallawa harunse wodho fushshate roorreenyi qoqqowu jeefisiisaanote amaale miniho.

ከሚመደብለት በጀት፣

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ፣

ሐ) ከሌሎች ምንጮች፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ከ (ሀ) እስከ (ሐ) ከተዘረዘሩት ምንጮች የሚገኘው ገቢ በድርጅቱ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ሆኖ የድርጅቱን ስራዎች ለማከናወን በየጊዜው ወጭ ይደረጋል፡፡

3. የድርጅቱ የገቢ እንደዚሁም የንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም በድርጅቱ የገንዘብና የንብረት አስተዳደር መመሪያና ማኑዋል መሠረት የሚፈጸም ሆኖ ማኑዋሉን የማሻሻልና የመቀየር ስልጣን የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ነው፡፡

**14. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1. ድርጅቱ የተሟላና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶችን ይይዛል፡፡

2. የድርጅቱ ሂሳብ በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም በውጭ ኦዲተሮች በየበጀት ዓመቱ ይመረመራል፡፡

**15. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>**

2. Loosu massago boorde konne lallawa loosu aana hosiisate hasiissanno biddissuwa fushshitara dandiitanno.

**16. <u>Lallawu Loosu Aana Hosanno Yanna</u>**

Kuni lallawi qoqqowu Amaale Mininni kajjino Maaja 7, 2012 M.D. hanafe loosu aana hosanno.

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma**

**Pirezidanticha**

1. ይህንን አዋጅ ተከትሎ ደንብ የማውጣት ስልጣን የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነው፡፡
2. የሥራ አመራር ቦርድ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**16. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ከሐምሌ 7 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**